የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፵<br>አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 14th Year No. 40<br>ADDIS ABABA 3rd June, 2008 |

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፬/፪ሺህ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሣይ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ...... ገጽ ፬ሺ፩፻፲፪

Proclamation No. 584/2008

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of French Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation Page 4112

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፬/፪ሺህ

## በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሣይ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሣይ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት እ.ኤ.አ. ጁን ፲፭ ቀን ፪ሺ፮ በፓሪስ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ - መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 584/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE FRENCH REPUBLIC FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME

**WHEREAS,** the Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income (the Convention) was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the French Republic in Paris on the 15th day of June 2006;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the agreement at its session held on the 15th day of May, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሣይ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፹፬/፪ሺህ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሣይ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፭ ቀን ፪ሺ፮ ፓሪስ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በግብር ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፮ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the French Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No. 584/2008".

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the French Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed in Paris on the 15th day of June 2006 is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to implement the agreement in collaboration with the concerned Government organs.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of June, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት